# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

16



"ሹብርን ለመቋቋም አብዮታችን ወደ አጥቂነት ደረጃ መሸጋገር አለበት።"

ታኅሣሥ ፲፰ — ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቁጥር ፬ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው።

# መደቦችና የመደቦች ትግል

## ፲፪ኛ ትምህርት ከን. ዓ.

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ብዙ ዓይነት ልዩነቶች አሉ ። ሰዎች በጾታ ይለያያሉ ። በቋንቋ ይለያያሉ ። በሃይማኖት ይለያያሉ ። በዕድሜ ይለያያሉ ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ኅብረተሰቡ እንደሚገኝበት ታሪካዊ ወቅት በበዝባዥና በተበዝባዥ ፤ በሀብታምና በደኃ ፤ ባጭሩ በመደቦች ይለያያሉ ። ለምሳሌ በሀገራችን ከላይ በጠቀስናቸው ልዩነቶች ላይ በአንድ በኩል ብዙ ችግረኞች በሌላ በኩል ደግሞ እፍኝ የማይሞሉ የተትረፈረፉ ሰዎች እናያለን ።

ብዙኃኑን ጾታ ሳይለይ ፤ ቋንቋ ሳይለይ ፤ ዕድሜ ሳይለይ ፤ ሃይማኖት ሳይለይ ፤ መድከም መሥራት ፤ መበዝበዝና መዋረድ ይጫናቸዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ በጾታ የተለያዩ ፤ በቋንቋ የተለያዩ ፤ በሃይማኖት የተለያዩ ፤ በዕድሜም የተለያዩ ሰዎች ይትረፈረፋሉ ። ብዙኃኑ በዚህ በሚደርስባቸው ብዝበዛና ጭቆና አንፃር ሲታይ በመሀከላቸው ያለው ልዩነት እስከዚህም ትልቅ ግምት የሚሰጠው አይደለም ። ተበዝባዥነታቸው ሌሎቹን ልዩነቶቻቸውን ወደኋላ አድርጎ ያስተሳስራቸዋል ። ለምሳሌ የኢትዮጵያን አብዮት ሁኔታ እንመልከት ። አሊሚራህ ፤ አስፋወሰን ፤ መንገሻ ሥዩም ፤ የሳውዲ አረብያ ንጉሥና አንድ የሲ.አይ.ኤ. ሹም በቋንቋ ፤ በሃይማኖት ፤ በባህል የተለያዩ ሰዎች ናቸው ። ነገር ግን ሁሉም የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ ልክ እንደ ወንድማማች ተባብረው ተጋግዘው ያሴራሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ልዩ ልዩ ሃይማኖት የሚከተሉ ፤ ልዩ ልዩ ባህል ያላቸው «ጭቁን» ኢትዮጵያውያን በነዚህ ልዩነቶች ሳይራራቁ ልክ እንደ ወንድማማች ተባብረው አብዮቱ እንዲገፋ ይታገላሉ ። ይህ የሚያሳየን የመደብ አንድነት ከቋንቋና ከሃይማኖት አንድነት ይበልጥ እንደሚያስተሳስር ነው ። ይህ የሚያሳየው በአንድ በበዝባዥና በተበዝባዥ በተከፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ዋናው ልዩነት በነዚህ ክፍሎች መሀከል ያለው የመደቦች ልዩነት ነው ማለት ነው ።

መደቦች በኅብረተሰብ ውስጥ እንዳሉ ሀብታምና ድኃ ፤ ጌታና ሎሌ እየተባለ እንደሚከፈል ማንም የሚያውቀው ነው ። ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት አገሮች ጥቂት ሀብታሞችና ብዙ ድኃዎች እንዳሉና ኅብረተሰባችን ውስጥ በመደቦች መከፋፈል እንዳለ ሊክድ የሚችል የለም ። «አላቻ ጋብቻ» ሀብታም ሲወድቅ ከሰገነት ፤ ድኃ ሲወድቅ ከመሬት» «ድኃ በጉልበቱ ባለጸጋ በሀብቱ» «ድኃና ጌታ ተሚግቶ ቅልና ድንጋይ ተማቶ» እነዚህ ሁሉ ተረቶች በሕብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ ግለሰቦች እንዳሉ የሚያመለክቱ ናቸው ። ይኸ ግልጽ ነው ።

ድኅነትና ሀብታምነት ለዘለዓለም እንደነበሩና ወደፊትም ለዘለዓለም እንደሚኖሩ ነገሮች ይታያሉ ። ልዩነቶቹም በሰው ፈቃድ ሳይሆን ከሰው ቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ አስመስሎ ለማቅረብ ሙከራ ይደረጋል ። ለምሳሌ «ይታደኋል እንጂ ይታገኋል ?» ይባላል ። በተጨማሪም የአርባ ቀን ዕድል የሚባለው አነጋገር ሰዎች ከመወለዳቸው የሚወሰንላቸው ቦታ እንዳለና እሱን ለመለወጥ ምንም ማድረግ እንደማይቻል ለማስረዳት የሚመክር አነጋገር ነው ።

እነማርክስ ይህን አስተሳሰብ ይዋጉታል ። ስለመደቦች አመጣጥና ስለወደፊት ዕድላቸው ከዚህ የተለየ አስተሳሰብ አላቸው ። በነማርክስ

አስተሳሰብ ሀብታምና ድኃ ፣ በዝባዥና ተበዝባዥ መደቦች ከዚህ በፊት ለዘለዓለም አልነበሩም ። ወደፊትም ለዘለዓለም አይኖሩም ። እንዲያውም የማርክስ ፍልስፍና በዚህ በኩል ያደረገው አስተዋጽኦ መደቦች በኅብረተሰብ ውስጥ መኖራቸውን መጠቆሙ አይደለም ። የመደቦች አመጣጥ ከአንድ ኅብረተሰብ ከታሪክ ዕድገት ጋር የተያያዘ በታሪክ ሂደት የሚጠፉ መሆኑን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተንትኖ ማሳየቱ ነው ። ማርክስ በዚህ ጉዳይ ላይ ዌድንሜየር ለተባለ ጓዱ የሚከተለውን ጽፎ እናገኘዋለን ።

« በኔ በኩል ግን በዘመኑ ኅብረተሰብ ውስጥ የመደቦችን መኖር አሳየሁ ተብዬ የምመሰገንበት ነገር የለም።. . . እኔ ያደረግሁት አዲስ ነገር ቢኖር ፩ኛ. የመደቦች መኖር በምርት ዕድገት ውስጥ ከተወሰኑ ታሪካዊ ወቅቶቹ ጋር የተያያዘ ነገር ብቻ መሆኑን ፤ ፪ኛ. በመደቦች መሀከል የሚደረገው ትግል የግድ ወደ ወዝ አደሩ አምባገነንነት የሚመራ መሆኑን ፤ ፫ኛ. ይህ የወዝ አደር አምባገነንነት ራሱ መደቦች ሁሉ ወደሚጠፉበት መደብ የለሽ ኅብረተሰብ መሸጋገሪያ መሆኑን ነው » ይላል ።

መደቦች ዘለዓለማዊ አለመሆናቸውንም ከፍ ብለን ባለፉት እትሞቻችን በቀረቡት የታሪክ ጥናቶች ተመልክተናል ። በጥንቱ የጋርዮሽ ሥርዓት መደቦች አልነበሩም ። በዚያን ዘመን እያንዳንዱ ሰው በጊዜው በነበረው የምርት መሣሪያ እየተጠቀመ የሚያመርተው ከእጅ ወደአፍ እንጂ ትርፍ ስላልነበረው ብዝበዛ አይቻልም ነበር ። ቀስ በቀስ ግን የምርት መሣሪያዎች እየተሻሻሉ ሲሔዱና ምርት እየጨመረ ሲሔድ አንዱ የአንዱን የሥራ ፍሬ ሊበዘብዝበት የሚችልበት ሁኔታ በመፈጠሩ ብዝበዛ ተጀመረ ። ቀስ በቀስ በዝባዥና መደቦች ስር እየያዙ ሄዱ ። ጥቂት ሰዎች የምርት መሣሪያዎች ባለቤት በመሆን ብዙኃኑን እያሰሩ በሠሪና በአሠሪ ፣ በበዝባዥና በተበዝባዥነት ላይ የተመሠረተ የምርት ግንኙነቶች ተፈጠሩ ።

«መደቦች በታሪክ በተወሰነ በአንድ ኅብረተሰብ የምርት ቅንብር (ሲስተም) ውስጥ በያዙት ቦታ ፤ ከምርት መሣሪያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት (ይህም አብዛኛውን ጊዜ በሕግ የተወሰነና የተጠበቀ) ሆኖ በኅብረተሰቡ የሥራ አደረጃጀት ውስጥ ባላቸው ሚና እና ከዚህም የተነሳ ከኅብረተሰቡ ሀብት ከሚያገኙት ድርሻ ብዛትና በማግኛውም ዘዴ የሚለያዩ ትላልቅ ግሩፖች ናቸው ። መደቦች በአንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ ኢኮኖሚ ቅንብር ውስጥ ከያዙት ቦታ የተነሳ አንዱ የሌላውን የሥራ ፍሬ ሊቀማ የሚችል የሰዎች ግሩፖች ናቸው ።

እንግዲህ የጋርዮሽ ዘመን ከፈረሰበት ጊዜ አንስቶ የምርት መሣሪያ ባለቤትነትን ከምርት የሚገኘውን ድርሻ . . . ወዘተ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመደቦች መሀከል የሚደረገው ትግል የኅብረተሰቦችን ታሪክ ወደፊት እያራመደ አምጥቶታል የዚህን የታሪክ አራማጅ የሆነ ትግል ዋናነት ለማመልከት ማርክስና ኤንግልስ ኮሚዩኒስት ማኔፌስቶች በሚለው የታወቀ ጽሑፋቸው መጀመሪያ ላይ የሚከተለውን አስፍረው እናገኛለን ።

« እስከ ዛሬ ድረስ ያለው የኅብረተሰብ ታሪክ ከጥንቱ የጋርዮሽ ሥርዓት በስተቀር የመደቦች ትግል ታሪክ ነው ። ባርያ ፈንጋይና ባርያ ፤ መኳንንትና ተራ ሰው ፤ ጌታና ሎሌ አሠሪና ሠራተኛ በአንድ ቃል ጨቋኝና ተጨቋኝ በማያቋርጥ አኳኋን አንዱ አንደኛውን በመቃረን አንዴ በስውር አንዴ በይፋ ያላቋረጠ ግጭት ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን ይህም ግጭት ወይ ኅብረተሰቡን አብዮታዊ በሆነ መንገድ እንደገና በማነጽ ወይም ደግሞ ሁለቱን ተቃራኒ መደቦች በማውደም አክትሟል ።

እንግዲህ አንድን ሕብረተሰብ ወደፊት የሚያራምደው በመደቦች መካከል የሚደረገው ትግል ነው ተባለ ። ከዚህ የሚገኘው አንድ የመጀመሪያ ሀቅ እንግዲህ ተራማጅ የሆነ ሁሉ የመደቦችን ትግል ማፋፋም እንጂ ማድበስበስ ወይንም ደግሞ ፈጽሞ ሊታረቁ የማይችሉ ተፃራሪ መደቦችን ለማስታረቅና ለማግባባት መሞከር የለበትም ማለት ነው ። ተራማጆች የመደቦችን ትግል ማፋፋም አለባቸው ሲባል የመደቦች ትግል የሚካሄድባቸውን ልዩ ልዩ መስኮች በደንብ ጠንቅቆ አውቆ በነዚህ ልዩ ልዩ መስኮች ያሉትን የተወሳሰቡ ግንኙነቶች ተገንዝቦ ፤ ለተበዝባዥ መደቦችም አስገንዝቦ እነዚህን መደቦች ለነዚህ ለተለያዩ መስኮች ትግል ብቁ አድርጎና አደራጅቶ ትግሉን መልክ አስይዞ በግንባር ቀደምነት መታገል አለበት ማለት ነው ።

ከሁሉ አስቀድሞ ግን ማንም ተራማጅ የመደቦችን ትግል ልዩ ልዩ መስኮች ከመዘርዘር በፊት የመደቦች ትግል « ሁለገብ » እንዲሆንና በአንድ በመደቦች በተከፋፈሉ ኅብረተሰብ ውስጥ ሕብረተሰብ ነክ ሆኖ ከዚህ ትግል ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይሳተፍ አስተሳሰብ ድርጅት ፤ አቋም እንደሌለ መገንዘብ ይኖርበታል ። አንድ ኅብረተሰብ በመደቦች ከተከፈለ በዚህ ሕብረተሰብ አባላት መሀከል በምንም ዓይነት ነገር ላይ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ የለም ። « ሰው ምን ይመስላል ቢለው ኑሮውን » እንዳለው ሁሉ እያንዳንዱ ሰው እንደየት ያስባል ቢባል እንደመደቡ ማለት ይቻላል ። በመሠረቱ በኢኮኖሚ ጥቅም ተፃራሪ ግጭት ስላለ ሕብረተሰብ ነክ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ ሁሉ ተፃራሪ መደቦች ተፃራሪ አቋም ይወስዳሉ ። ከአንዱ መደብ ሙሉ በሙሉ እውነት የሆነ ነገር ሌላው ተቃራኒው መደብ ሙሉ በሙሉ ውሸት ይሆናል ። አንዱ መደብ ጥሩ ነው ብሎ የሚያስበው ለሌላው መደብ መጥፎ ይሆናል ። ከዚህ በፊት ያነሳነውን የአብዮት ምሳሌ እንውሰድ ። መሳፍንቱና አድኃሪ መደቦች አብዮትን «መጥፎ ነው ሞት ነው » ብለው ይገምታሉ ። ሰፊው ሕዝብ ደግሞ «አብዮት ሕይወት ነው » ብሎ ያምናል ።

ከየመደብ ጥቅማቸው አንፃር ሲታይ ሁለቱም ልክ ናቸው ። ለአድኃሪዎች አብዮት ሞት ነው ። ለሰፊው ሕዝብ ደግሞ አብዮት ሕይወት ነው ። ስለሆነም አንድ ሰው ኅብረተሰብ ነክ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ አንድ ሰው ተነስቶ ሐሳቡን ሲገልጽ « ልክ ነው ወይስ ልክ አይደለም » የሚለው ጥያቄ እስከዚህም ሊያስጨንቀን አይገባም ። ጥያቄው ይህ ሰው የሰነዘረው ሐሳብ የማንን መደብ ጥቅም ያንጸባርቃል የሚል መሆን አለበት ። ለምሳሌ « ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት » የሚባለው መፈክር ሲነሣ አብዮታውያን ይኽ «መፈክር ልክ ነው ወይስ ስሕተት ነው ? » የሚል ጥያቄ ውስጥ አይገቡም ። ይህ መፈክር የየትኛውን መደብ ጥቅም ያንጸባርቃል የሚለውን ጥያቄ አንስተው የአድኃሪዎችን ጥቅም የሚያንጸባርቅ እንደሆነ ይረዳል ። ስለሆነም ነገሩን ከመደብ አንፃር በመመልከት «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የቀልባሾች መፈክር ነው » ይላሉ ።

አጥፊና ጠፊ በሆኑ መደቦች በተከፈለ ሕብረተሰብ ውስጥ በመደቦች መሀከል ያለውን ሁለገብ የሆነ መለያየት ለማሳየት «ታጠቅ» የተባለው መጽሔት የሚከተለውን ጽፎ ነበር ።

«በአንድ ሀገር በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ይቆራኙ እንጂ ድኃና ሀብታም እኮ የሚኖሩት» ሁለት ዓለም ውስጥ ነው ። የሕዝብ ነፃነት አለ ። የበዝባዦች ነፃነት አለ ። የሕዝብ እውነት አለ ። የበዝባዦች እውነት አለ ። የሕዝብ ፍትሕ አለ ። የበዝባዦች ፍትሕ አለ ። የሕዝብ ደህንነት አለ ። የበዝባዦች ደህንነት አለ ። የበዝባዦች መብት ሕዝብን መጨቆን ነው ። የሕዝብ መብት ደግሞ የነሱን ጭቆና ተናንቆ መጣል ነው ። ነፃነታቸው ከሁሉ አስቀድሞ እንደልብ የመዝረፍ ነፃነት ነው ። የሕዝቡ ነፃነት ደግሞ ከሁሉ በፊት ዘረፋን መቋቋም ነው ። የበዝባዦች ሀብት መሠረቱ የሕዝቡን ላብ መግፈፍ ነው። የሕዝብ ሀብት መሠረቱ ሁሉም የላቡን ፍሬ አለመነፈጉ ነው ። ባጭሩ ለሕዝቡና ለበዝባዦች አንድ ዓይነት ትርጉም የሚሰጠው ምንም ዓይነት ቃል የለም ። ስለዚህም በበዝባዦች ሥርዓት ውስጥ በአንድነት « የሁሉም» ጥቅም የሚጠበቅበት ምንም ዓይነት ተአምር ሊኖር አይችልም ። ዛሬ የነሱ ነፃነት የሕዝብ ባርነት ነው ። ነገ የሕዝብ ነፃነት የነሱ መደምሰስ ይሆናል ። »

(ታጠቅ ዓለም አቀፍ የኢት. ተ. ማ. በአውሮጳ የኢት.ተ. ማኅበር የተዘጋጀ ሰኔ ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. )

ይህ ሁለገብ የሆነና ጠቅላላ የመደቦች ግጭት ግን በጣም በተያያዙና በተወሳሰቡ ሦስት መልኮች ሊጠቃለል ይችላል ። እነሱም የኢኮኖሚ ትግል ፤ የፖለቲካ ትግልና የርዕዮተ ዓለም ትግል ናቸው ። በመጀመሪያ ከሁሉ ግልጽ የሆነውና የግጭቶቹ ፤ የትግሎቹ መሠረት የሆነው የኢኮኖሚ ግጭትና የጥቅም ትግል አለ ።

ይህ የኢኮኖሚ ግጭት ከሁሉ በቅድሚያ ጎልቶ የሚታይ ትግል ነው ። ለምሳሌ በደመወዝ ጭማሪ ፤ በሥራ ሁኔታ መሻሻል . . . ጉዳይ ላይ